# የ2024 ሲያትል ቴክኖሎጂ ተደራሽነት ሪፖርት:- ቁልፍ ግኝቶች

"ለሁሉም የሲያትል ነዋሪዎች ማካተት፣ የትምህርት ስኬት እና ኢኮኖሚያዊ ብልጽግናን ለማረጋገጥ፣ እኛ ደግሞ ዲጂታል ፍትሃዊ እኩልነት ለሁሉም መጣር አለብን።"

*– Mayor Bruce Harrell*

## ይህ የዳሰሳ ጥናት ስለ ምን ነበር?

የሲያትል ከተማ ነዋሪዎች ቴክኖሎጂን እና ኢንተርኔትን እንዴት እንደሚጠቀሙ ለመረዳት ፈልጎ ነበር። ከ4,600 በላይ ሰዎች ስለ የሚከተሉት ለማወቅ የዳሰሳ ጥናት አድርገዋል:-

- የኢንተርኔት መዳረሻ ያላቸው እነማን ናችው
- ሰዎች የሚጠቀሙባቸው መሣሪያዎች ምን ምን ናቸው
- ሰዎች ቴክኖሎጂን የሚጠቀሙት በምን ያህል ምቾት ነው
- ሰዎች በመስመር ላይ እንዳይገቡ ምን ምን እንቅፋቶች ያግዷቸዋል

## የኢንተርኔት መዳረሻ ያላቸው እና ማን ናቸው

- 98% የሚያህሉ የሲያትል ቤተሰቦች በቤት ውስጥ ኢንተርኔት መጠቀም ይችላሉ (ይህ ከ2018 95% ከፍ ብሏል)
- ሆኖም፣ አንዳንድ ነዋሪዎች መስመር ላይ የመግባት ተግዳሮቶች ያጋጥሟቸዋል:-

- ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ሰዎች
- እንግሊዝኛ እንደ የመጀመሪያ ቋንቋቸው የማይናገሩ ሰዎች
- አካል ጉዳተኝነት ያላቸው ሰዎች
- ጥቁር እና የአሜሪካ ተወላጅ ነዋሪዎች
- አረጋውያን

## የኢንተርኔት ዋጋው በተደራሽነት እና በአጠቃቀሙ ላይ ተጽእኖ ያሳድራል

- አብዛኛዎቹ ቤተሰቦች ለኢንተርኔት በወር ቢያንስ $100 ዶላር ይከፍላሉ
- አማካይ ገቢ ያላቸው ቤተሰብ 2.2% የሚያጠፉ ስሆን፣ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ቤተሰቦች ከገቢያቸው 5% የሚሆነውን ያህል በኢንተርኔት ላይ ያወጣሉ
- ብቃት የሚያሟሉ ቤተሰቦች በኢንተርኔት አገልግሎት ገንዘብ እንዲቆጥቡ ሊያግዙ የሚያስችሉ ፕሮግራሞች አሉ፣ ነገር ግን ብዙ ሰዎች ስለእነሱ አያውቁም ወይም እየተጠቀሙባቸው አይደሉም።

## በሲያትል ውስጥ ሰዎች የሚጠቀሙባቸው መሣሪያዎች ምንድን ናቸው

- ሁሉም ቤተሰቦች ማለት በሚቻልበት ደረጃ (95%) የእጅ ስልኮች/ ስማርትፎኖች አሏቸው
- 86% ያህሉ ጭን ላይ የሚደረግ ኮምፒዩተር/ ላፕቶፕ አላቸው
- 67% ታብሌቶች አሏቸው
- አንዳንድ ቤተሰቦች ለመሥራት፣ ለማጥናት ወይም አገልግሎቶችን ለማግኘት አስቸጋሪ ሊያደርግ የሚያደርጉ፣ እነዚህን መሣሪያዎች በቤተሰብ አባላት መካከል መጋራት ይኖርባቸዋል

## ሰዎች ዲጂታል ችሎታዎች ይፈልጋሉ እና ተጨማሪም ያስፈልጋቸዋል

- 60% የሚያህሉ የሲያትል ነዋሪዎች መሰረታዊ ዲጂታል ተግባሮችን ሁሉ ለመስራት ምቾት ይሰማቸዋል
- ብዙ ሰዎች ስለ የሚከተሉት የበለጠ ማወቅ ይፈልጋሉ:-

- የግል መረጃቸውንበመስመር ላይ ማስጠበቅ
- መሰረታዊ የኮምፒውተርችሎታዎች
- ሶፍትዌሮችን እና መተግበሪያዎችንመጠቀም
- ስራዎችን በመስመርላይ መፈለግ

# ወደኋላ የቀረ ማን ነው

**የዳሰሳጥናቱ እንደሚያመለክተው እነዚህ ከታች የተመለከቱ ቡድኖች ቴክኖሎጂን በመጠቀም ረገድ የበለጠ ችግሮች ያጋጥሟቸዋል:-**

- **በዕድሜ የገፉ አረጋውያን**
- **አካል ጉዳተኝነት ያላቸው ሰዎች**
- **እንግሊዝኛ እንደ የመጀመሪያ ቋንቋቸው የማይናገሩ ሰዎች**
- **ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ሰዎች**
- **ጥቁር እና የአሜሪካ ተወላጅ ነዋሪዎች**

# ስለዚህ ጉዳይ ሲያትል የምታደርግ

**ከተማዋየሚከተሉትን ለማድረግ እየሰራች ነው:-**

1. **ለዲጂታል ተደራሽነት ፕሮግራሞች ተጨማሪ ድጋፍ ለማግኘት እነዚህን ግኝቶች በስፋት ማከፋፈል**
2. **ስለ ኢንተርኔት ቅናሽ ፕሮግራሞች ሰዎች እንዲያውቁ እና እንዲመዘገቡ መርዳት**
3. **ሰዎች የሚያስፈልጋቸውን መሳሪያዎች እንዲያገኙ ማገዝ**
4. **ስልጠና እና ድጋፍ ለመስጠት ከማህበረሰባዊ ድርጅቶች ጋር መስራት**
5. **ሰዎች በቴክኖሎጂ እርዳታ እንዲያገኙ የበለጠ ቀላል ማድረግ**
6. **በከተማዋ በመላ ዲጂታል ተደራሽነትን ለማሻሻል ጠንካራ የህዝብ እና የግል ሽርክናዎችን መገንባት**

# ይህ ለምን አስፈላጊ እንደሆነ



**አስተማማኝየኢንተርኔት አገልግሎት ተደራሽነት መኖር እና ቴክኖሎጂውን እንዴት መጠቀም እንዳለብን ማወቅ ለሚከተሉት ነገሮች አስፈላጊ እየሆነ መጥቷል:-**

- **ለስራ**
- **ለትምህርት ቤት**
- **ለጤና እንክብካቤ**
- **ለመንግስት አገልግሎቶች**
- **ከቤተሰብ እና ከማህበረሰቡ ጋር እንደተገናኙ ለመቆየት**
- **መረጃ እና የማወቅ ሀብት ምንጮችን ለማግኘት**

**ከተማዋእየጨመረ በመጣው በኛ ዲጂታል አለም ውስጥ እያንዳንዱ ሰው ለመሳተፍ የሚያስፈልጉት መሳሪያዎች እና ክህሎቶች እንዳሉ ማረጋገጥ ትፈልጋለች። በዚህ የዳሰሳ ጥናት ውስጥ ተሳትፎ ላደረጋችሁት ብዙ የማህበረሰብ አባላት እናመሰግናለን።**

Seattle Information Technology

**የከተማዋበዲጂታል የማካተት ስራ ላይ መከታተል ይቻላል**
**www.seattle.gov/tech**